# ፍታዊ መኖሪያ እና ማረፊያዎች

# ተከራዮች፡ መብቶቻችሁን እወቁ!

## በሚከተሉት ምክንያቶች ከመኖሪያ ቤትዎ ሊከለከሉ ወይም ሊባረሩ **አይችሉም** ...

| ዘር ፣ ብሄር ወይም ብሄራዊ አመጣጥ | አካል ጉዳተኝነት | ሃይማኖት | የቤተሰብ ሁኔታ | የጾታ ማንነት ወይም የወሲብ ዝንባሌ |
|---|---|---|---|---|

**በርስዎ ላይ ይሄ ከተከሰተ ፣ የማስወጣት መብት ጋር በመደወል ምክር ያግኙ ።**



## ፍትሃዊ የመኖሪያ ህግ ምንደን ነው?

ፍትሃዊ የመኖሪያ ህግ የፌደራል ህግ ሲሆን **ተከራዮችን ከአድሎ ይከላከላል**። **በዘር ፣ ብሄር ፣ ብሄራዊ አመጣጥ ፣ አካል ጉዳተኝነት ፣ ሃይማኖት ፣ ቤተሰብ ሁኔታ ፣ የጾታ ማንነት ፣ ወይም የወሲብ ዝንባሌን** ባተኮረ መልኩ አከራዮች አድሎ እንዳያደርጉ **ህገወጥ** ያደርግባቸዋል።

**የመኖሪያ ችግር ላላቸው ሰዎች ቅድሚያ በመስጠት ማከራየት በህግ ይፈቀዳል!**

**አብዛኞቹ መኖሪያዎች በፍትሃዊ የመኖሪያ ህግ ጥላ ስር የተሸፈኑ ናቸው ፤ ነገር ግን አንዳንድ ያልተሸፈኑ የተወሰኑ ጉዳዮች አሉ።**

**በህጉ ያልተሸፈኑ የመኖሪያ አይነቶች መካከል**

- ባለይዞታው የሚኖርባቸው 4 እና ከዛበታች ብዛት ያላቸው ቤቶች
- ያለ ደላላ የተከራዩ የአንድ ቤተሰብ መኖሪያዎች
- ለአባላቶቻቸው በድርጅቶች አማካኝነት የሚስተዳደሩ መኖሪያዎች

## በፍትሃዊ የመኖሪያ ህግ መሰረት ህገወጥ የሆነው የቱ ነው?

ክላይ በተነሱት ምድቦች መሰረት አከራዮ **የማይችሏቸው**

- **ለርስዎ አለማከራየት**
- **ለማመልከት እንዳይችሉ መከልከል ወይም ለመኖሪያ ያመለከቱትን ማመልከቻ መከልከል**
- **ለርስዎ የተለየ መመሪያ ወይም ክፍያ ከሌሎች ተከራዮች በተለየመልኩ መወሰን**
- **መኖሪያው እያለ እንደሌለ መናገር**
- **የተወሰኑ መኖሪያዎችን እንዲክራዩ ወይም ሌሎችን እንዳይከራዩ ለማስገደድ መሞከር**



ነገር ግን የሚከተሉትን ከአድሎነት ጋር በማይገናኙ ምክንያቶች ማድረግ የሚችሏቸው ፤ ለምሳሌ፣ ዝቅተኛ የክሬዲት ነጥብ ካሎ ፣ ማመልከቻዎን መከልከል ውይም ረከስ ያለ መኖሪያን እንዲከራዩ ማሳመን መሞከር ይችላሉ።

**አከራዮ የፍትሃዊ መኖሪያ ህግን እየጣሱ እንደሆነ ካሰቡ ኢአርቲሲ ወይም የቴነሲ የፍትሃዊ መኖሪያ ሸንጎ ጋር በ (615) 874-2344 ይደውሉ።**

**hud.gov/fairhousing/fileacomplaint ን በመጠቀም ቅሬታዎን ያስገቡ።**

**AMHARIC — FAIR HOUSING**

LEGAL AID SOCIETY OF MIDDLE TENNESSEE AND THE CUMBERLANDS (833) 837-HOME | AMAC American Muslim Advisory Council (615) 988-6460 | conexión américas (615) 701-7957

ይህ መረጃ ለዴቪድሰን ካውንቲ ብቻ ነው። እዚህ የቀረበው መረጃ የህጋዊ ምክር አይደለም ለመሆንም አይሞክርም። ማንኛውም የህግ ችግር ካሎ የግል ጠበቃዎን ወይም የአቅራቢያዎን የመሃል ቴነሲ እና ከምበርላንድ ቢሮ ህግ ድጋፍ ሶሳይቲ በ 1-800-238-1443 ጋር ይደውሉ. ወይም የናሽቪል ሂስፓኒክ ጠበቆች ህብረት ጋር በ 1-615-701-7957. 9/23 የተሻሻለ።

# ፍታዊ መኖሪያ እና ማረፊያዎች

# ተከራዮች: መብቶቻችሁን እወቁ!

## ምክንያታዊ/ተገቢ መኖሪያዎች እና ማሻሻያዎች ምንድን ናቸው?



**ምክንያታዊ/ተገቢ መኖሪያዎች** ማለት አካል ጉዳተኛ ተከራዮች የሚኖራቸው የመኖሪያ ስፍራ መመቻቸትን እና ቤታቸውን መጠቀም እንዲችሉ **በህጎች እና አገልግሎቶች ላይ የሚደረጉ ለውጦች** ናቸው። አንዳንድ ምሳሌ ሊሆኑ የሚችሉ ፡-

- የቤት ኪራይ **ወር በገባ በ 1 ከመክፈል ይልቅ በ15 እንዲከፍሉ** መፍቀድ፤ ምክንያቱም የሶሻል ሲኪውሪቲ የአካል ጉዳተኛ ገቢ (SSDI) ቼክ እስከ 14ተኛው ቀን ድረስ ስለማይሰጥ።
- **የስነልቦና ደጋፊ የቤት ወይም የአገልግሎት እንስሳቶችን ያለ ክፍያ ይዞመኖር** እንዲቻል መፍቀድ ፤ ምንም እንኳን መኖሪያው የቤት እንሣትን የሚከለክል ፖሊሲ ቢኖረውም።



**ምክንያታዊ ማሻሻያዎች** ማለት **በመኖሪያው ላይ አካላዊ ማሻሻያዎችን** በማድረግ ለመኖር እና ለመጠቀም ምቹ ማስቻል ማለት ነው። ይህን ምክንያታዊ ማሻሻያ ለማስፈጸም **ገንዘብን** የሚያስወጣ ከሆነ አብዛኛውን ግዜ **ተከራዩ** ከፍሎ የማሰራት እናም ለቆ ሲሄድ የማስነሳት ሃላፊነት አለበት። አንዳንድ ምሳሌ ሊመስሉ የሚችሉ ፡-

- **በመታጠቢያ ቤት ውስጥ እጀታ ማስገጠም** ወይም መንቀሳቀስን የሚያግቱ የአካል ጉዳቶችን በተመለከተ በደረጃ ላይ የመደገፊያ ሬሊንግ ማስገጠም።
- ወደ መኖሪያዎ በዊልቼር ለመግባት በቤቶ ፊት በር ላይ **ራምፕ ማስገጠም**።

ቤት አቅራቢዎች ሌላ መኖሪያዎችን ማመላከት ይችላሉ ፣ ነገር ግን የርስዎን ጥያቄ ምክንያታዊ እና አስፈላጊ እስካልሆነ በስተቀር

**አከራዮ ለምክንያታዊ/ተገቢ መኖሪያ እና ማሻሻያ የሚያቀርቡትን ጥያቄ ውድቅ ካደረገ የማስወጣት መብት ጋር በመደወል ያማክሩ።**

## ምክንያታዊ/ተገቢ መኖሪያ ወይም ማሻሻያን እንዴት መጠየቅ እችላለሁ?

ምክንያታዊ/ተገቢ መኖሪያ ወይም ማሻሻያን ለመጠየቅ የተሻለው መንገድ ለመኖሪያዎ አስተዳዳሪ ምን አይነት ለውጦችን እንደሚያስፈልግዎ በማብራራት **በደብዳቤ አስፍሮ** ማስገባት ነው።

አካል ጉዳትዎ በግልጽ የማይታይ ከሆነ የመኖሪያ አስተዳዳሪዎ የጉዳትዎን ማስረጃ መጠየቅ ይፈቀድላቸዋል ፤ ነገር ግን የርስዎ የህክምና ማህደር ወይም ዝርዝር መረጃዎት አያስፈልጋቸውም። የአካል ጉዳትዎን የሚመለከት ማስረጃ ስለ እርስዎ ጉዳይ ከሚያውቁ የህክምና አገልግሎት ሰጪ ፣ የአገልግሎት ኤጀንሲ ወይም ከሌላ ሶስተኛ ወገን ሊገኝ ይችላል።

**ምክንያታዊ/ተገቢ መኖሪያ ወይም ማሻሻያን ሲጠይቁ እርዳታ ካስፈለገዎ ኢአርቲሲ ወይም ፍትሃዊ የመኖሪያ ሸንጎ ጋር ይደውሉ።**

**AMHARIC -- FAIR HOUSING**

LEGAL AID SOCIETY OF MIDDLE TENNESSEE AND THE CUMBERLANDS (833) 837-HOME | AMAC American Muslim Advisory Council (615) 988-6460 | conexión américas (615) 701-7957

ይህ መረጃ ለዴቪድሰን ካውንቲ ብቻ ነው። እዚህ የቀረበው መረጃ የህጋዊ ምክር አይደለም ለመሆንም አይሞክርም። ማንኛውም የህግ ችግር ካሎ የግል ጠበቃዎን ወይም የአቅራቢያዎን የመሃል ቴነሲ እና ከምበርላንድ ቢሮ ህግ ድጋፍ ሶሳይቲ በ 1-800-238-1443 ጋር ይደውሉ. ወይም የናሽቪል ሂስፓኒክ ጠበቆች ህብረት ጋር በ 1-615-701-7957. 9/23 የተሻሻለ።